# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

**በስመ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ አሐዱ አምላክ፤**
**በስመ እግዝእትነ ወእምነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ::**

ይድረስ፡- ለአቃሲኒ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ዘካርያስ ከተማ (ሰኞ ገበያ)፤ ታች ነገላ።

በሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በእናት አገራችንና ቅድስት ንግሥታችን፡ ድንግል ማርያም ስም፡ ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን፤ እግዚአብሔር ይመስገን እኛ ደኅና ነን።

ባለፉት ስምንት ዓመታት፡ ለደብረ ብርሃናት ቅዱሳን ሓዋርያት፥ ለጋርጥብና መድኃኔ ዓለም፥ ለአውችንድባ ቅዱስ ገብርኤል፥ ለጩጫ ቅዱስ ሚካኤል፥ ለሳዕም ቊስቋምና ለጉድባ ቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤዎች ስንጽፍ፡ ለእናንተም፡ የእነዚህኑ ደብዳቤዎች ግልባጭ በመላክ፡ ማናቸውንም፡ ቊምነገር እንድታውቁት ማድረጋችንን ታስታውሱታላችሁ።

በታች ነገላ፡ ቀበሌ ፳፫ ውስጥ ለተጠቃለሉትና የአለቃ ዘካርያስ ቅኚዎች ለኾኑት፡ ለሰባቱ ሰበካዎች፡ ልናበረክተው ላሰብነው የአገልግሎት አስተዋጽዖዋችን መመሪያ እንዲኾነን፡ ተስማምተን ያጸደቅነውን የተግባር ሥርዓታችንን፡ ቀደም አድርገን፡ በመጀመሪያ፡ በታኅሣሥ ፲፮ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም.፥ ኋላም በማከታተል፡ ከላይ በተጠቀሱት የደብዳቤ ግልባጮች አማካይነት፡ በተብራራ መልኩ፡ እንድትረዱት ስላደረግን፡ የዚህን መመሪያ ምንነት፡ ኹለንተናውን፡ በትክክል እንደተገነዘባችሁት እናምናለን።



መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekw@ethkogserv.org
Website: www.ethkogserv.org
Facebook: ethiopiathekingdomofgod

ይኸውም፡ ስሞቻቸው፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ ሌሎቹ መሰሎቻችሁ የሰበካ ጉባኤዎች፡ ቀደም አድርገው በጽሑፍ እንዳረጋገጡልን ኹሉ፡ በእርግጥ፡ እናንተም፡ እንደነርሱ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ ጸንታችሁ፥ አምልኳችሁን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ለመፈጸም፥ በእውነተኛው ቊርጥ ንስሓችሁም፡ እየራሳችሁን፡ ለሥጋወደሙ ለማብቃትና የጀመራችሁትን፡ የመልካም ሕይወት ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ ወደፊት፡ አጠናክራችሁ በመቀጠል ለመኖር መወሰናችሁ ነው።

አዎን! ከዚህ በፊት፡ በየጊዜያቱ በጻፍናቸውና ከላይ፡ ቀደም ብለው በተወሱት ደብዳቤዎች አማካይነት እንደተብራራላችሁ፥ እናንተም፥ እኛም፡ በተስማማንበት፡ በዚያ መመሪያ መሠረት፡ ኹላችንም፡ በያለንበት፡ ግዳጃችንን አውቀን እንደፈጸምንና እንደምንፈጽም በመተማመን፡ ዓቅማችን የፈቀደውን፡ የበኩላችንን አስተዋጽኦ፡ አኹን ደግሞ፡ እነሆ ልከንላችኋል።

ያ መመሪያ ከያዛቸው ፍሬ ነገሮች መካከል፡ ዋና ዋናዎቹን፡ አኹንም፡ እዚህ ላይ እንጠቅሳቸው ዘንድ፡ እጅግ አስፈላጊ ኾኖ አግኝተነዋል፤ በኹላችንም ዘንድ፡ ሊታሰቡና ሊፈጸሙ የሚገባቸው፡ እነዚሁ ፍሬ ነገሮች፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

አንደኛው፡ ለቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎቹ እድሳት፥ ደግሞም፡ ሊሠሩ ለታቀዱት ትምህርት ቤትና የከተማ ኹለገብ አዳራሽ፥ እንዲሁም፡ ለወደፊት የሚወጡ ሌሎች የልማት ተግባራት ቢኖሩ፡ ለእነዚያ ኹሉ፡ እኛ፡ በበኩላችን፡ ዓቅማችን በፈቀደ፡ ከምናደርገው አስተዋጽኦዋችን በላይ የሚኾነውን፥ የቀረውንና የጎደለውን፡ አስፈላጊና ተጨማሪ ወጪ፡ በተናጠልም ኾነ በኅብረት ማሟላት ያለበት፡ የየሰበካው ሕዝብ፡ በበኩሉ በሚያደርገው አስተዋጽኦ መኾኑን የሚያመለክተው ነው።

ኹለተኛው፡ ይህ፡ በእኛ በኩል፡ እስካኹንና አኹንም የተደረገው የገንዘብ አስተዋጽኦ የተገኘው፡ ከሌላ አምጥተንና ሰብስበን ሳይኾን፡ የቤተሰባችን አባሎች የኾንነው፡ እኛና ልጆቻችን፡ እያንዳንዳችን፡ እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋና በረከት፥ አካልና ጤንነት፥ ሙያና ዕድል፡ እየራሳችን፡ በግል ሠርተን ካፈራነው ጥሪት ብቻ መኾኑን የሚያስታውቀው ነው።

ሦስተኛው፡ እንዲህ፡ በንጹሕ ድካምና በራስ ወዝ ተገኝቶ የተላከው ይህ፡ የእኛ የገንዘብ አስተዋጽኦ፡ ከየሰበካው ሕዝብ ከሚሰበሰበው ጋር ተዳምሮ፡ በሙሉ፡ የእግዚአብሔር ገንዘብ ስለኾነ፡ ያም፡ ለዚያው፡ ለተመደበለት፡ ለእግዚአብሔር መልካም አገልግሎት ሊውል ስለሚገባ፥ እንዲያ ካልኾነ ደግሞ፡ በነፍስ በሥጋም፡ ጽኑ ፍዳን ስለሚያስከትል፡ ባለፈው ጊዜ፡ በሌላ ኹኔታ እንደታየው፡ ገንዘቡ እንዳይባክን፥ ወይም፡ ለሌላ ዓላማና ጥቅም እንዳይውል፡ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚያስፈልግ መኾኑን የሚያስጠነቅቀው ነው።

አራተኛው፡ በአገልግሎታችን በኩል፡ እስካኹን ያበረከትነውና ወደፊትም የምናበረክተው፡ የአስተዋጽኦዋችን ዋና ዓላማ፡ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት የተባልነው፡ እናንተም፥ እኛም፡ እያንዳንዳችን፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርንና በተሟላው የተፈጥሮ ጸጋዎቹ የታደልን መኾናችንን አውቀን፥ ከፈጣሪያችን ካገኘነውና ከምናገኘው በቀር፡ በግልም ኾነ በጋራ፡ ከማንም ፍጡር፡ እርዳታና ምጽዋት ሳያስፈልገን፥ ሳንጠይቅም፡ ራሳችንን ችለን ልንኖር የሚገባን መኾናችንንም ተገንዝበን፥ ለዚህ ከፍተኛ፡ የሕይወት ደረጃና ሰብአዊ ክብር፡ እየራሳችንን አብቅተን መገኘት፡ ከኹላችንም የሚጠበቅብን መኾኑን፡ በአትኩሮት የሚያስገነዝበው ነው።

በዚህ ኹኔታ፡ ሥራው በጥሩ ይዘት እንደሚከናወን የምንተማመንበትን፡ የሰበካችሁን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የእድሳት ሥራ ለማስፈጸም ይረዳችሁ ዘንድ፡ የበኩላችን አስተዋጽኦ የኾነውን፡ ፲ሺ (አሥር ሽህ) ብር፡ ይኸው ልከንላችኋል።

አኹንም፡ ቢኾን፡ የሰበካችሁ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እድሳት ሥራ፡ በዚያ መመሪያ መሠረት፡ ተካኺዶ የተፈጸመ መኾኑን ለማሳየት፡ የእኛ ተጠሪዎች፡ ቄስ ጌቴ አበባው ሙጨና ጸሓፊው አቶ ወንድሙ መለሰ፥ እንዲሁም፡ የእናንተን ሰበካ ጉባኤ ጨምሮ፡ ሰባቱ ሰበካ ጉባኤዎች በአባልነት የሚገኙበት፡ ያ፡ አጠቃላይ ሕዋስ፡ በቅድሚያ አውቆትና ተስማምቶበት፡ የሰጠው ውሳኔ፡ በእኒሁ ተጠሪዎቻችን አማካይነት፡ አስቀድሞ፡ ለእኛ ሊደርሰን ይገባልና፡ ይህንኑ እንዲፈጸም ታደርጉ ዘንድ፡ በአክብሮት እናሳስባችኋለን።

አምላከ ንዋየ ክርስቶስ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ረድኤትና በረከት፡ ለሰባቱ የአለቃ ዘካርያስ የነገላ ሰበካዎች፡ ያሰብነውንና የወጠንነውን፡ ይህን የአገልግሎት ዕቅድ፡ እስከዚህ ለማድረስ እንዳስቻለን ኹሉ፡ ለመጨረሻው መልካም ፍሬ እንዲያበቃልን፡ መለኮታዊ ፈቃዱ ይኹንልን!

ጥቅምት ፩ ቀን፥ ፳፻፳ ዓ. ም.

በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ስም፡-

---

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ

ግልባጭ፦

ለደብረ ብርሃናት ቅዱሳን ሓዋርያት (አቦ) ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጋርጥብና መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለአውችንድባ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጨጫ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለሳዕም ቍስቋም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤
ለጉድባ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤

ለቄስ ጌቱ አበባው ሙጨ፤
ለአቶ ወንድሙ መለሰ፤
በነገላ፡ የአገልግሎታችን ተጠሪዎች።
ዘካርያስ ከተማ (ሰኞ ገበያ)፤ ታች ነገላ።